የወላጆች ኃላፊነቶች

በፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሂደት ወላጆች ትጉህ ተሳታፊዎች ናቸው።
የወላጆች ኃላፊነቶችም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

❧

በIFSP ሂደት ሙሉ ተሳትፎ ማድረግ—ለልጃቸው የሚሆኑ ግቦችን ለማቀድና ግቦቹንም በስራ ላይ ለማዋል ከአገልግሎቱ አቅራቢዎች ጋር መስራትና ተመክሮና ግምገማዎቻቸውንም ለአገልግሎቱ አቅራቢዎች ማጋራት።

❧

የልጃቸው የአገልግሎት አቅርቦት ላይ ተጽዕኖ ስለሚያደርጉ ሁኔታዎች ለአገልግሎቱ አስተባባሪ ኢንፎርም ማድረግ (ማሳወቅ)።

❧

የቀጠሮ ሰዓትን አክብሮ መገኘት፤ በቀጠሮ ለመገኘት የማይችሉበት ሁኔታ ሲኖርም ለአገልግሎት አቅራቢው ቀደም ብሎ ማሳወቅ።

❧

ሁሉም ቤተሰቦች የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ይሆኑ ዘንድ፤ አገልግሎቱ በሚሰጥበት አካባቢ የሚገኙትን ሰዎችና በጠቅላላ አካባቢውን ጭምር ማክበር።

ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን ይፈልጋሉ? እንግዳውስ ቀጥሎ የተመለከቱት ማጣቀሻዎች ስለቅድመ-ጣልቃገብነት ዘዴ የወላጆች መብቶች የበለጠ ኢንፎርሜሽን ይሰጡዎታል።

- *ህልሞችና ተፈታታኝ ጥያቄዎች፡ የቤተሰብ መመሪያ ስለሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ ባይ ሕጻናት ፕሮግራም።*
- የአካል ጉድለት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ድንጋጌ ክፍል C
- ክፍል 303፤ የፌደራል ህግጋቶቄች ደንብ ርዕስ 34
- ክፍል 300፤ ንዑስ ክፍል 560-577፤ የፌደራል ህግጋቶች ደንብ ርዕስ 34
- ክፍል 99፤ የፌደራል ህግጋቶች ደንብ ርዕስ 34

የነዚህን ሰነዶች ቅጂ ለማግኘትቄ፤ ቀጥሎ በተመለከቱት አድራሻዎች ይጠይቁ፤

የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል
የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት፤
Maryland Infants and Toddlers Program
200 West Baltimore Street; Baltimore, MD 21201
(410) 767-0261 በድምጽ • (800) 535-0182 የድምጽ ነጻ ጥሪ
(410) 333-8165 ፋክስ • (410) 333-0731 TDD

Robert L. Ehrlich, Jr.
ገዢ

Edward L. Root
ፕሬሲደንት፤ የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ቦርድ

Nancy S. Grasmick
የክፍለ-ግዛቱ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

Carol Ann Baglin
ረዳት የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ
የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት

የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል፤ ለቅጥር ሥራም ሆነ ፕሮግራምን ለመጠቀም፤ በዘር፤ በቀለም፤ በጾታ፤ በእድሜ፤ በትውልድ ወይም ብሄር፤ በሃይማኖት፤ ወይም በአካለ-ጎደሎነት ላይ የተመሰረተ ልዩነት አያደግም። የዲፓርትሜንቱን ፖሊሲ በተመለከተ ጠይቆ ለመረዳት፤ የዕኩልነት ዋስትና አስከባሪ ቅርንጫፍን በሚከተሉት አድራሻዎች ያነጋግሩ። Equity Assurance and Compliance Branch 410-767-0246 በድምጽ 410-333-2226 ፋክስ፤ ወይም 410-333-6442 TDD. ✦ ይህ ሰነድ ከዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ክፍል፤ የልዩ ትምህርት ክፍልና የማህበራዊ ባህሪያት ማረሚያ ቢሮ፤ IDEA፤ ክፍል C፤ እርዳታ #H181A020124. ✦ በተገኘ ገንዘብ፤ በልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ቅርንጫፍ አማካኝነት ተቀነባብሮ የታተመ ነው። ✦ በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹት አመለካከቶች የግድ የዩናይትድ ስቴትስን የትምህርት ክፍል ወይም የማንኛውንም ሌላ የፌደራል ኤጀንሲን አመለካከት የሚያንጸባርቁ ላይሆኑ ይችላሉ፤ ስለሆነም በዚህ መልኩ መታየት የለባቸውም። ኢንፎርሜሽኑ ከህትመት ባለቤትነት የመብት ገደብ (ኮፒ ራይት ነጻ) ነው። አንባቢዎች ቅጂውን እያባዙ እንዲያዳርሱና እንዲያስነብቡት ይበረታታሉ፤ ነገርግን፤ እባከዎ ይህ ሰነድ፤ በሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ቅርንጫፍ የስራ ውጤት ለመሆኑ ተገቢውን ዋጋ ይስጡ። ✦ የአካል ጉድለት ያለባቸው አሜሪካዊያን ድንጋጌ(ADA)ን በሚመልከት ሲጠየቅ፤ ይህ ሰነድ በሌላ የተለየ አማራጭ አቀራረብ ተዘጋጅቶ ይገኛል። የልዩ ትምህርት ክፍሉን በሚቀጥሉት አድራሻዎች ያነጋግሩ፤ 410-767-0261 በድምጽ፤ 410-333-2661 ፋክስ፤ 410-333-0731 TDD.

3/04



በፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓት የወላጆች መብቶችና ኃላፊነቶች

የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል
የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት፤
የሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ የሚሉ ልጆች ፕሮግራም

Amharic

ለሜሪላንድ የፈጥኖ ጣላቃ ገብነት ስርዓት የመሰረት ድንጋይ የሆነው፣ የአካል ጉድለት ያለባቸውን ለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ በማለት ላይ ያሉ ልጆችን ለመርዳትና እድገታቸውንም ለማፋጠን፣ በቤተሰቦችና በባለሙያዎች መካከል ያለው ቀና ትብብር ነው። ይህ ተጓዳኝነት፣ በቤተሰብ ላይ ያተኮረ ግለሰባዊ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅዶች (IFSPs) የሚዳብሩና የሚያድጉበት ዋነኛው መሰረት ነው።

ሁለቱም፣ የIDEA (የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ድንጋጌ) ክፍል C እና የሜሪላንድ ህግጋቶች ደንብ 01.04.01፣ በፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ወላጆችን የተወሰኑ መብቶች ያረጋግጣሉ።

ይህ የጽሁፍ መግለጫ፣ ወላጆች ስለልጃቸውና ቤተሰባቸው የሚቀርቡ አገልግሎቶችን እስመልክቶ የሚኖራቸው ሃሳብና ምርጫ እንደሚሰማና እንደሚከበር የሚያረጋግጠውን፣ እንደዚሁም ወላጆች እነዚህን አገልግሎቶች ማዳረስን በተመለከተ በሚደረጉ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ የሚጫወቱትን ብርቱ ሚና አስመልክቶ በቂ ኢንፎርሜሽን የማግኘት እድል ያላቸው መሆኑን በማካከተት ጭምር፣ እነዚህን መብቶች አጠር-አጠር ባሉ ዝርዝሮች ያብራራል።

እያንዳንዱ በሜሪላንድ የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓት ውስጥ የሚሳተፍ ቤተስብ፣ በጥቅል ዝርዝር ሁኔታ የወላጆችን መብት የሚዘረዝረውን *የህልሞችና ተፈታታኝ ጥያቄዎች፦ የቤተሰብ መመሪያ ስለሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ ባይ ሕጻናት ፕሮግራም* የሚለውን ቅጂ ያገኛል።

በሜሪላንድ የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓት መሰረት፣ ወላጆች የሚከተሉትን ለማድረግና ለማግኘት መብት አላቸው።

- *በመመዘን፣ በመገምገም እና የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት አቅርቦትን በሚመለከት ስምምነታቸውን ይሰጣሉ።*

ልጃቸውና ቤተሰባቸው አገልግሎቶችን እንዴት እንድሚያገኙ ኃላፊነት የተሞላበት ውሳኔ ለማድረግ ይቻላቸው ዘንድ፣ ወላጆች የሚፈልጉትን ኢንፎርሜሽን ማግኘት ይገባቸዋል። ወላጆች ሌሎች አገልግሎቶች በንም መልኩ ሳይጨናገፉባቸው፣ በክፍለ-ግዛቱ ህግ መሰረት የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት አላቸው።

- *የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሪኮርዶችን የማግኘትና ሪኮርዶቹም እንዲስተካከሉ የመጠየቅ።*

ወላጆች የልጃቸውን የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሪኮርድ የማየት መብት አላቸው። ወላጆች፣ ስለልጃቸው የተቀመጠው የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሪኮርድ የተሳሳተ ኢንፎርሜሽን አለበት ወይም አሳሳች ነው ብለው ካመኑ፣ ሪኮርዱ እንዲስተካከል መጠየቅ ይችላሉ።

- *በፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓቱ አማካኝነት የቀረበውን መብታቸውን በሚመለከት ማስታወቂያ የማግኘት።*

ወላጆች ስለመብታቸው ግልጽ፣ ሊረዱት የሚችሉ ዓይነት ኢንፎርሜሽን ማግኘት ይኖርባቸዋል። በፈጥኖ ጣልቃ ገብነቱ ሂደት በሚኖራቸው ተሳትፎ ሁሉ፣ ስለግምገማዎችና አገልግሎቶች መጀመር፣ ወይም የለውጥ ሃሳብ ስለመቅረቡ በሚመለከት፣ ውላጆች በራሳቸው የመጀመሪያ ቋንቋዎቻቸው ተመጣጣኝ የሆነ ማስታወቂያ ሊደርሳቸው ይገባል።

- *የግለሰባዊ ኢንፎርሜሽን ምስጢራዊነቱ ተጠብቆ እንዲቀመጥ የመፈልግ።*

ማንኛውም ዓይነት የግለሰባዊ መለያ እንፎርሜሽን ከፈጥኖ ጣልቃ ገብነትና ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ከመጋራቱ በፊት፣ ወላጆች የሚስማሙ መሆናቸውን በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ያለወላጆች ስምምነት ኢንፎርሜሽንን ማውጣት የሚፈቀደው በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ነው።

- *በሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ በማለት ላይ ያሉ ልጆች ፕሮግራም (MITP) አቤቱታ (ቅሬታ) ማስመዝገብ።*

ወላጆች፣ በፈጥኖ ጣልቃ ገብነቱ ውስጥ በሚሳተፉበት በማንኛውም ጊዜ ውስጥ፣ (1) ስለልጃቸው የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት የማግኘት/አለማግኘት መብት የተሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ፣ (2) የልጃቸውን ምዘና ወይም ግምገማ በተመለከተ፣ (3) ለልጃቸው የሚቀርበውን አገልግሎት በተመለከተ፣ ወይም (4) ለልጃቸው ስለሚቀርበው አገልግሎት ያለባቸውን ገንዘባዊ ኃላፊነት በተመለከተ የማይስማሙ ከሆኑ የጽሁፍ አቤቱታቸውን (ቅሬታቸውን) ለMITP ማስመዝገብ (ማቅረብ) ይችላሉ።

- *ደንብን የተከተለ አቤቱታቸው በገለልተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል እንዲታይላቸው የማድረግ።*

በወላጆች ሲጠየቅ፣ አቤቱታዎችን (ቅሬታዎችን) ለመበየን (ለመፍታት)፣ የድርድር ችሎት እና/ወይም ገለተኛ ጉዳይ ሰሚ ችሎት ይካሄዳል። እነዚህን ሂደቶች ለሚመለከት የበለጠ ኢንፎርሜሽን፣ ከሕላምሙ ማግኘት የሚቻለውን፣ *ድርድርና ገለልተኛ የአቤቱታዎች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት* የሚለውን ጽሁፍ ይመልከቱ።